የ2021 የኮሎራዶ ሕግ አውጪ አካል አጠቃላይ ስብሰባ
ስደተኛን ያካተቱ አስፈላጊ የሕግ ረቂቆች

- ለውይይት የቀረበ የተወካዮች ምክር ቤት የሕግ ረቂቅ **21-1054** (ሴኔተር ጁ ጎንዛሌስ እና ተወካይ ዲ ጃክሰን)፦ ይህ የሕግ ረቂቅ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ያሉ ሰዎች ያካባቢውንና የስቴት የመኖሪያ እርዳታ ማግኘት መቻላቸውን ያረጋግጣል። አንዳንድ የመኖሪያ መርሃ ግብሮች የተወሰኑ የስደተኛ ሁኔታዎችን የሚጠይቁ የፌዴራል የብቃት መስፈርቶች ሊኖሯቸው ቢችሉም፥ ሰነድ አልባ ግለሰቦችና ቤተሰቦች የተረጋጋ መኖሪያ አገልግሎቶች የማግኛ ዕድላቸው የተሻለ ይሆናል።

- ለውይይት የቀረበ የሴኔት ሕግ ረቂቅ **21-077** (ሴኔተር ጁ ጎንዛሌስ እና ተወካዮች ኤ ቤኔቪዴዝ፥ ሲ ኪፕ)፦ የስደት ሁኔታ ካሁን በኋላ ለስቴትና ለአካባቢ ፈቃዶች፥ የምስክር ወረቀቶች ወይም ምዝገባ የብቁነት መስፈርት አይሆንም። የዚህም ምሳሌዎች የCertified Nursing Assistants (የተረጋገጠላቸው የነርስ ረዳቶች) ወይም የንግድ ሥራ ፈቃዶችን ዓይነት ፈቃዶችን ያካትታሉ። ይህ ለውጥ በሕጋዊ መንገድ የማይኖሩ የኮሎራዶ ሰዎችን በሙሉ ይመለከታል፥ እንደ DACA ተቀባዮች ዓይነት የሥራ ፈቃድ ያላቸውን ጨምሮ።

- ለውይይት የቀረበ የሴኔት ሕግ ረቂቅ **21-009** (ሴኔተር ኤስ ጃኬዝ እና ተወካይ ዋይ ካራቬዎ)፦ አዲስ መርሃ ግብር በመፍጠር፥ የኮሎራዶ ነዋሪዎች፥ የመኖሪያ ሰነድ የሌላቸውን ጨምሮ፥ ለእራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው የሚበጀውን ማቀድ እንዲችሉ የወሊድ መቆጣጠሪና የምክር አገልግሎት ያገኛሉ።

- ለውይይት የቀረበ የሴኔት ሕግ ረቂቅ **SB 21-131** (ሴኔተር ጁ ጎንዛሌስ እና ተወካይ ጎንዛሌስ-ጉቲዬሬዝ)። ለስቴት መርሃ ግብሮችና አገልግሎቶች፥ ለመንጃ ፈቃድ ጨምሮ ማመልከቻ የሚያስገቡ ሰዎችን መረጃ ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ያስችል ዘንድ፥ በሕግ ወይም በፍርድ ቤት በተሰጠ የፍርድ ቤት ማዘዣ በኩል ካልተጠየቀ በስተቀር የስቴት ተቋሞች የግል መለያ መረጃን ለስደተኞች ሕግ ማስከበሪያ ሲባል ይፋ ማድረግ አይችሉም። የስቴት ተቋሞች የጋራ መረጃ ቋቶችን መዳረሻ ከመስጠታቸው በፊት የምስክር ወረቀቶች ማግኘት፥ የስደተኛ ሁኔታን በተመለከተ የሚሰበሰብ መረጃን ከአስፈላጊው ውጪ እንዳይሰበሰብ ውስን ማድረግና አዲሱን ሕግ ማክበራቸውን ለማረጋገጥ መደበኛ ሪፖርቶች ማስረከብ አለባቸው።

- ለውይይት የቀረበ የተወካዮች ምክር ቤት የሕግ ረቂቅ **21-1150** (ሴኔተር ጁ ጎንዛሌስ እና ተወካይ አይ ጆዴ)። በDepartment of Labor and Employment (የሥራና ቅጥር መምሪያ) ውስጥ አዲስ የኮሎራዶ **Office of New Americans** (የአዲስ አሜሪካውያን ቢሮ) መቋቋሙ ከስደተኛ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ከፍ ተደርገው በስቴቱ መንግሥት መፍትሄ እንዲያገኙ ያደርጋል። የሕግ ረቂቁ የማህበረሰብ አማካሪ ኮሚቴን በመፍጠር ስደተኞች ፍትሃዊ የዕድሎች ተጠቃሚዎች መሆናቸውን ለማረጋገጥ በማህበረሰብ ላይ የተመሠረተ የድርጅት መሠረተ ልማት ላይ ኢንቬስትመንት ማድረግ ላይ ያተኩራል።

- ለውይይት የቀረበ የተወካዮች ምክር ቤት የሕግ ረቂቅ **21-1194** (ሴኔተር ዲ ሞሬኖ እና ተወካዮች ኬ ቲፐር፥ ኤን ሪክስ)፦ የኢሚግሬሽን የሕግ ጥብቅና ፈንድ የኢሚግሬሽን ሂደቶች ላይ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ግለሰቦች በነጻ አገልግሎቶችና ጥብቅና የማግኘት ዕድላቸውን ያሰፋውና የስደተኞች ማቆያ ውስጥ ላሉና በስቴቱ ገጠራማ አካባቢዎች ከአገር መባረር ለገጠማቸው ሰዎች ቅድሚያ ይሰጣል። የOffice of New Americans ይህን የነጻ የሕግ ምክርና ውክልና ለማቅረብ በዚህ ፈንድ በኩል በኮሎራዶ ውስጥ ለሚገኙ ለትርፍ ላልተቋቋሙ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል።

- ለውይይት የቀረበ የተወካዮች ምክር ቤት የሕግ ረቂቅ **21-199** (ሴኔተሮች ኤስ ጃኬዝ ሉዊስ፥ ኤፍ ዊንተርና ተወካዮች ዲ ኤስጋር፥ ኤስ ጎንዛሌስ-ጉቲዬሬዝ)። በዕድሎች ላይ ፍትሃዊነትን ለመፍጠር እንዲያስችል፥ ከጁላይ 1 2022 ዓ.ም. ጀምሮ በሕጋዊ መንገድ መገኘት በፌዴራል ሕግ ሥር ለተፈቀዱት ለአንዳንድ የስቴትና የአካባቢ የሕዝብ ጥቅማጥቅሞች መስፈርት አይሆንም። ይህ በSB 21-077 እና በHB 21-1054 ሥር የሚገኙትን ከማግኘት ባሻገር ያስፋፋዋል።

- ለውይይት የቀረበ የተወካዮች ምክር ቤት የሕግ ረቂቅ **21-1057** (ሴኔተሮች አር ሮድሪጌዝ፥ ጀ ኩክ፥ ተወካዮች ኬ ቲፐር፥ ዲ ሮበርትስ)። በአሁኑ ሕግ መሠረት ገንዘብ ወይም ሌሎች ውድ ዕቃዎችን ለመስረቅ የሌላ ሰው የስደተኛ ሁኔታን ሪፖርት አደርጋለሁ ብሎ ማስፈራራት ወንጀል ነው። በተጨማሪም አንድን ሰው አንድ ነገር ለማስደረግ (ወይም ላለማስደረግ) የስደተኛ ሁኔታን ሪፖርት አደርጋለሁ ብሎ ማስፈራራትም ወንጀል ነው።

- ለውይይት የቀረበ የተወካዮች ምክር ቤት የሕግ ረቂቅ **21-1075** (ሴኔተር ጂ ጎንዛሌስ እና ተወካይ ኤስ ሎንቲን)። ቃላት ወሳኝ ናቸው። የሕግ ረቂቁ በአገልግሎት ውሎች ውስጥ ሕገወጥ መጤ የሚለውን መግለጫ ያስወግድና "ፈቃድ የሌለው ሠራተኛ" በሚለው ይተካዋል።

- ለውይይት የቀረበ የሴኔት ሕግ ረቂቅ **21-233** (ሴኔተሮች አር ሮድሪጌዝ እና ሲ ሃንሰን፥ ተወካዮች ኤ ቤናቪዴዝ፥ ኤስ ጎንዛሌስ-ጉቲዬሬዝ)። ብዙ ሕጋዊ መኖሪያ የሌላቸው ስደተኞች በስደተኛ ሁኔታቸው ምክንያት ብቻ የሥራ አጥ እርዳታ የማግኘት ብቃት የላቸውም። ይህ ረቂቅ ሰነድ የሌላቸው የኮሎራዶ ኗሪዎች በስቴታችን ውስጥ የሥራ አጥ ጥቅማጥቅሞች ውስጥ ቢካተቱ ምን እንደሚመስል ለመረዳት የሚያስችል ጥናት ለማካሄድ ይረዳል።

- ለውይይት የቀረበ የተወካዮች ምክር ቤት የሕግ ረቂቅ **21-1060** (ሴኔተር ጂ ጎንዛሌስ እና ተወካዮች ኤስ ጎንዛሌስ-ጉቲዬሬዝ እና አይ ጆዴ)። የ"ዩ ቪዛ" በፌዴራል ኢሚግሬሽን ሕግ መሠረት የተወሰኑ የወንጀል ተጎጂዎች ስደተኞች በሕጋዊነት ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ የሚወስዱበትን መንገድ ይሰጣል። ብቃት ያላቸው አመልካቾች ግለሰቡ ተጎጂ ነበር፥ እንዲሁም ወንጀሉን ለመመርመር ወይም በክሱ ላይ እያገዘ ነው ወይም አግዟል የሚል ከሕግ አስከባሪ የመጣ የምስክር ወረቀት ሊኖራቸው ያስፈልጋል። ይህ ረቂቅ ሕግ አስከባሪ ተቋሞች በሙሉ ማረጋገጫውን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲያሟሉ ያስደርጋል፥ እንዲሁም ከግምት ውስጥ የሚገቡ ጉዳዮችን ይዘረዝራል፥ የግል መረጃን ከኢሚግሬሽን ባለሥልጣኖች ይከላከላል፥ እንዲሁም ሕግ አስከባሪዎች ለተጎጂዎች ስለ ዩ ቪዛ መንገራቸውን ያረጋግጣል።

- **SB 21-087** (ሴኔተሮች ጂ ዴኒየልሰን እና ዲ ሞሬኖ እና ተወካዮች ኬ ማኮርሚክ እና ዋይ ካራቬዖ)። ይህ ረቂቅ የአንድ ሰው የስደተኛ ሁኔታን ከግምት ውስጥ ሳይከት የግብርና ሠራተኞች ሌሎች ሠራተኞች ካሏቸው ጥበቃዎች ጋር ተመሳሳይ ጥበቃዎች እንዲኖራቸው በማድረግ የተስፋፋ የAgricultural Workers' Rights (የግብርና ሠራተኞች መብቶች) ይፈጥራል - ለምሳሌ የተረጋገጠ መነሻ ክፍያና የትርፍ ጊዜ ክፍያ፥ የምግብና የእረፍት ጊዜ፥ የመደራጀት መብት፥ በሠራተኛ መኖሪያ ውስጥ ጎብኚ መቀበል እና ከመጠን በላይ ሥራና የጤና ጥበቃዎችን ማግኘት።